# ለቅሶ እንድረስ



-በአበራ ለማ

ቀብር ውጡ ወዳጆቼ - ጌታ ብእር አረፈ
ደራሲው ሰው ሆነ - ፈጣሪነቱን ተገፈፈ፤
በመጋኛ ተቦትልኮ - በዘር ሀረግ ተጠርንፎ
ጌታ ብእር ተሻረ - ካባ ማእረጉን ተገፎ
የት ይደርሳል ያልነው ኀበዝ - ተስፋ ያልነው ሽል ጨንግፎ፤

ቀብር ውጡ ወዳጆቼ - ልባችሁ ባዘን የቆሰለ
ፈጣሪው ሰው ሁኖ - ብጤ ፈጣሪን ከሰለለ፤
የብእር አምላክ ቢቆጣ - በየቤቱ ቢገነፍል
ዘረ ማንዘር ብሎ ነገር - የብእር ጌታን ሲገድል
ማን ይችላል ወዳጆቼ  - ማን ይዳኛል ይህን በደል?

ቀብር ውጡ ወዳጆቼ - እግዚኦ ብቻ ነው ’ሚበጀው
ለካስ ብእርም ይሞታል - ፈጣሪ አምላኩ ሲበድለው
ደራሲ ፈጣሪነቱን ትቶ - የዘር እርሻ ካረገው፤
ቡዳ ቤት ሰላቢ ገባ - ብእር ተረታ በሞቱ
ፈጣሪም ሰው ሆነ - ሰው ለሥጋው በማድላቱ፤

ቀብር ውጡ ወዳጆቼ - የብእር ሞት የቆጫችሁ
የቦለቲካ ሾተላይ - ስልጡን ብእሩን  የነሳችሁ፤
የብሩህ ቀለሙ ጌታ - የጥበብ እስትንፋሱ መገኛ

ወጣቱ መልከ ጻዴቅ - ወዳጇ ልቤው ብእረኛ፤

ነገሩ ሁሉ ከሆነ - ጌታም ለሥጋው አደላ

ሰውነቱን ማወቅ እንጂ - ፈጣሪነቱማ ተከላ፤

የጥሁፋችን መጣምር - የጥበብ ጌጡ ተስፋ

እንዲህ ተመንገድ ቀርቶ - ተጃችን ላይ ታንቀላፋ፤

ለቅሶ እንድረሲ ኀበዝ - ዓለም ሲያሳየን ገመና

የብእር ሞትን እያየን - ለማንም አይበጅ ጽሞና፤

አዎን... ፈጣሪው ሰው ሆነ - ለሥጋ ሥጋው እያደላ

ብእር ሥጋ ሆነ - ሰው ሥጋውን እየበላ፤

የዘር ቦለቲካን እንርገም - የተስፋን ብእር ለማዳን

ከዘር ጥላቻ እንመንጥቀው - ይድን ይሆናልና አንድ ቀን፤

ቀብር እንውጣ ወዳጆቹ - ለብእር ሞት እናልቅሰው

ጥላቻን እንጥላው -

ደረት መተን፤ ሙሾ ሞሸን እንቅበረው፤

(ablemma@gmail.com)